**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: קיץ תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 005384**

**תרגום לאמהרית (6)**

# תורה שבעל פה

דינים ומבוא — שאלון לעולים חדשים

## הוראות לנבחן

א. <u>משך הבחינה</u>: שעה וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שני פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (16x4) — | 64 נקודות |
| פרק שני | — | (12x3) — | 36 נקודות |
| סה"כ | — | | 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי־לועזי / לועזי־עברי.

ד. <u>הוראות מיוחדות</u>: אין.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>. רשום "טיוטה" בראש כל עמוד המשמש טיוטה.
כתיבת טיוטה בדפים שאינם במחברת הבחינה עלולה לגרום לפסילת הבחינה.

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ጊዜ፦ የ2019 ዓ.ም. የበጋ ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 005384**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# የቃል መጽሐፍ ቅዱስ

ፍርድ እና መግቢያ — ለአዲስ ገቢዎች መጠይቅ

## ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

א. <u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ አንድ ሰዓት ተኩል።

ב. <u>የፈተናው መዋቅርና ነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሁለት ምዕራፎች ይዟል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (4x16) — | 64 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (3x12) — | 36 ነጥብ |
| በአጠቃላይ | | — | 100 ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. <u>ልዩ መመሪያ</u>፦ የለም።

<u>በመጠይቁ ደብተር ላይ ብቻ</u> ጻፍ። ለማሰቢያ በምትጠቀምበት ገጽ መግቢያ ላይ በሙሉ "טיוטה" ብለህ ጻፍበት።
ከመጠይቁ ደብተር ውጭ በሆነ ወረቀት ላይ ማሰቢያ መጻፍ ለፈተናው ውድቅ መሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢሆኑም ለወንድም ለሴትም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

# ጥያቄዎቹ

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-5 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አራቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 16 ነጥብ)።

**1.** የቃል መጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ (מבוא לתורה שבעל פה)

ሀ. የኢየሩሳሌም ታልሙድ (התלמוד הירושלמי) ለምን በዚህ ስም እንደሚጠራ አብራራ።

(4 ነጥብ)

ለ. (1) የራብ ሞሼ ቤን ማይሞን (ራምባም)ን የሐይማኖታዊ መመሪያ ጽሑፎች (חיבור ההלכתי) ሁለት ስሞችን ጥቀስ።

(2) ከእነዚህ ስሞች ውስጥ አንዱን አብራራ።

(8 ነጥብ)

ሐ. ራምባም በሐይማኖታዊው መመሪያ ጽሑፎች መግቢያ ላይ ይህ የመመሪያ ጽሑፍ ሁለት ችግሮችን ለመፍታት እንደሚጠቅም ጽፈዋል።

ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ አንዱን አብራራ። (4 ነጥብ)

**2.** የተፈቀዱ ሐይማኖታዊ መመሪያዎች (הלכות כשרות)

ሀ. (1) በግማራ መሠረት፣ "ማር ኡክባ" ሥጋ ነክ ምግቦችን ከተመገበ በኋላ የወተት ነክ ምግቦችን ለመመገብ የሚጠብቀው ጊዜ "ከማዕድ እስከ ማዕድ" ("מסעודה לסעודה") ነው ብለዋል።

ለማር ኡክባ አነጋገር ሁለት ትርጉሞችን (ማብራሪያዎችን) ጻፍ።

(2) ሺራ ሥጋ ነክ ምግቦችን ከተመገበች በኋላ የወተት ነክ ምግቦችን ለመመገብ ስድስት ሰዓት ትጠብቃለች።

በ13፡00 ሰዓት ሥጋ በልታ አበቃች እና በ15፡00 ሰዓት ስለ ማዕዱ የምስጋና ጸሎት (ברכת המזון) አደረገች።

ሺራ በስንት ሰዓት ነው ወተት ነክ ምግብ መብላት የሚፈቀድላት? መልስህን አስረዳ።

(8 ነጥብ)

ለ. በፊትህ የሁለት ሁኔታዎች መግለጫዎች ቀርበዋል። ሥጋ ነክ ምግቦችን ከተመገቡ በኋላ ወተት ነክ ምግቦችን ለመመገብ መጠበቅ ያለበትን ጊዜ በተመለከተ በቀረቡት ሁኔታዎች በእያንዳንዳቸው ምን ማድረግ እንደሚገባ ጻፍ።

(1) አንድ ሰው ከሥጋ ጋር የበሰለ ድንች ተመግቦ ከጨረሰ በኋላ ወተት ነክ ምግብ መመገብ ይፈልጋል።

(2) አንድ ሰው በሥጋ ማብሰያ ድስት የተበሰለ ድንች (ያለ ሥጋ) ተመግቦ ከጨረሰ በኋላ ወተት ነክ ምግብ መመገብ ይፈልጋል።

(8 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

3. ጸሎት (תפילות)

ሀ. በቋም የሚጸለየው የዘወትር ጸሎት ሦስት ክፍሎች አሉት።

(1) ሦስቱ ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ ጻፍ።

(2) ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ፥ ከአንዱ ክፍል ሦስት ቡራኬዎችን ጥቀስ።

(9 ነጥብ)

ለ. በቋም ከሚጸለየው ጸሎት ላይ በዓመት ውስጥ በተወሰኑት ቀናት ላይ ተጨማሪ አለ። እንደነዚህ ዓይነት ሁለት ተጨማሪ ጸሎቶች ጥቀስ እና ከእነሱም እያንዳንዳቸው በየትኞቹ የዓመቱ ቀናት ላይ እንደሚጨመሩ ጻፍ። (7 ነጥብ)

4. ሰንበት

ሀ. በሰንበት ቀን ምን ዓይነት ምግብ "ፐላታ" (פלטה) ላይ ማስቀመጥ ይፈቀዳል? በምን ዓይነት መስፈርትስ ነው? (6 ነጥብ)

ለ. (1) "מוקצה מחמת גופו" ምን እንደሆነ አብራራ እና ለዚህ ዓይነት "ሙቅጼ" አንድ ምሳሌ ጻፍ።

(2) "מוקצה מחמת גופו"ን ለማንቀሳቀስ ወይም ለማዘዋወር የሚፈቀድበትን አጋጣሚ ግለጽ።

(10 ነጥብ)

5. ሞአዲም — ፋሲካ

ሀ. (1) በፋሲካ ምሽት (ליל הסדר) "ማሮር" የሚበላበት ምክንያት ምንድን ነው?

(2) "ማሮር"ን ከ"ሃሮሴት" ውስጥ መንከር ምክንያቱ ምንድን ነው?

(7 ነጥብ)

ለ. (1) በፋሲካ ምሽት ለ'ሃሳባ" ትዕዛዝ (מצוות ההסבה) ምክንያት ምንድን ነው?

(2) በፋሲካ ምሽት በ'ሃሳባ" የሚፈጸሙ ሁለት ትዕዛዛትን ጥቀስ።

(9 ነጥብ)

/ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል/

## **ምዕራፍ ሁለት** (36 ነጥብ)

ከ6-9 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ — 12 ነጥብ)።

**6.** በሰው እና በጓደኛው መካከል ያሉ ሐይማኖታዊ መመሪያዎች (הלכות בין אדם לחברו)

**א.** (1) አስተማሪ የተማሪን ንብረት ሊነጥቀው የሚፈቀደው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

(2) የተማሪን ንብረት የነጠቀው አስተማሪ – በዚህ ንብረት ምን ማድረግ ነው የማይፈቀድለት?

(6 ነጥብ)

**ב.** አንድ የተሸከርካሪ ባለቤት ወይም ሹፌር በሌሎች ላይ ጉዳት ላለማድረስ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ሁለት ድርጊቶችን ጻፍ። (6 ነጥብ)

**7.** ቡራኬዎች — (ברכות)

**א.** (1) አንድን ሰው የመጀመሪያ ቡራኬ እንዲያደርግ የሚያስገድደው የምግብ መጠን ምን ያህል ነው?

(2) አንድን ሰው የመጨረሻ ቡራኬ እንዲያደርግ የሚያስገድደው የምግብ መጠን ምን ያህል ነው?

(6 ነጥብ)

**ב.** (1) "שהחיינו" ቡራኬ የሚባረክበትን አንድ አጋጣሚ ጻፍ።

(2) "הגומל" ቡራኬ የሚባረክበትን አንድ አጋጣሚ ጻፍ።

(6 ነጥብ)

**8.** ሰንበት

**א.** (1) "ברכת מעין שבע" በሰንበት የምሽት ጸሎት ላይ ይባላል።

ይህ ቡራኬ ለምንድን ነው በዚህ ስም የተጠራው?

(2) በሰንበት ምሽት ከ"ኪዱሽ" በፊት ከሚደረጉ ልማዶች ውስጥ አንዱን ጻፍ።

(6 ነጥብ)

**ב.** በ"ኪዱሽ" ጊዜ ዳቦው ለምን መሸፈን እንዳለበት አብራራ። (3 ነጥብ)

**ג.** በሰንበት ቀን የምግብ ቡራኬዎች ላይ የሚጨመር አንድ ተጨማሪ ቡራኬ ጻፍ። (3 ነጥብ)

**9.** ትዕዛዛት (מצוות)

**א.** የሚከተሉትን እገዳዎች እያንዳንዳቸውን አብራራ፦ ለሰው መጥፎ ስም መስጠት (הוצאת שם רע)፣ ክፉ ንግግር (לשון הרע)፣ ሐሜት (רכילות)። (9 ነጥብ)

**ב.** የ"אונאת דברים" እገዳ ምንድን ነው? (3 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

**בהצלחה!**

መብቱ ለእስራኤል መንግሥት የተጠበቀ ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።
זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך